የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር - ዴሞክራሲያዊ ምትሕብባር ትግራይ

TIGRIAN ALLIANCE FOR NATIONAL DEMOCRACY (TAND)
e-mail: ezanareg@hotmail.com

# አብረን እንቁም ፣ ተማሪም አይከፋፈል

ኢህአዴግ ለ14 ዓመታት ያጨማለቀው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ጭራሽ እርቃኑን ስላስወጣው አሁን በትግራይ ህዝብና ወጣት ልጆቹ ጉያ ውስጥ ተወሽቆ ለመሰንበት አድኑኝ እያለ ነው ። "ያለኔ አለኝታ የለህምና ደግፈኝ ፤ ካልደገፍከኝ ጥፋትህ የሚመኙ ኃይሎች እየመጡብህ ነው" በማለት ሰንካላ የጥላቻ ፖለቲካ እንደ ዋና ስልት አድርጎ "ቀቢጸ-ተስፋ" ጭሆት እያሰማ ይገኛል ። የትግራይ ህዝብ ግን ምንም እንኳ ድርብርብ አፈና ቢበዛበት ፣ ከወገኑ ከመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጎን ቆሞ በቃን ውረድ እያለው በመሆኑ ትንሽ መተንፈስ የቻለው የአዲስ አበባ ነዋሪ የትግራይ ህዝብ ባለፈው ምርጫ በማያሻማ ሁኔታ አረጋግጦለታል ። ከዚህም በተጨማሪ ትግራይ ውስጥ ምርጫውን መቶ በመቶ አሸነፍኩበት እያለ ቢያምቧርቅም ፤ ከምርጫው ማግስት የህወሓት ማእከላዊ ኮሚቴ አባል አቶ ዓባይ ወልዱ መቀሌ ውስጥ በመገኘት በከተማው የሚገኙትን የቢሮና የመምሪያ ሓላፊዎችን ሰብስበው፣ የምርጫውን ሁኔታ ለመቃኘት ባካሄዱት ስብሰባ ላይ "የትግራይ ህዝብ አልጠላንም፣ ችግሬን ይፈቱልኛል ብሎ መርጦናል" ሲሉ ተሰብሳቢው ደግሞ "እነሱን ካልመረጥኩ የት እገባለሁ በሚል ፤ አማራጭ ማጣትና አደጋ ይደርስብሀል የሚለው ቅስቀሳ በፈጠረው ፍርሀት እንደሆነ እንጂ ህወሓት ችግሬን ሰምቶ ይፈታልኛል ብሎ እንዳልሆነ ገልፀዋል" ሲል ሪፖርተር ጋዜጣ በግንቦት 28 ቀን 1997 ዓ.ም እትሙ ዘግቦት የሚገኘው እውነታ የትግራይ ህዝብ ህወሓትን እንዴት እንደጠላና እንደተፋው የሚያሳይ መረጃ ነው ። ትግራይ ውስጥ አንድ ተቃዋሚ ድርጅት ገብቶ እንዳይወዳደራቸው መከልከል ራሱ ጉዳቸው እንዳይወጣ የተቀናጀ የአምባገነኖች ሴራ መሆኑ ማን ይስተዋል ?

ከላይ የተጠቀሱ የተወሰኑ ጭብጦች ህወሓት ከትግራይ ህዝብ እንዴት እንደተነጠለ በግልጽ ያሳዩናል ። የህወሓት መሪዎችም ከመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ ሳይሆን ታጋች አርገው ይዘውት የቆዩት የትግራይ ህዝብም እንዴት እንደተፋቸው በሚገባ ተገንዝበውታል ። በዚህ ምክንያትም ዛሬ የትግራይ ህዝብ ከሌላው ወገኑ የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር አብሮ ለመብት ፤ ለዴሞክራሲና ለፍትሕ እንዳይታገል በመከልከል ሳይወሰኑ ፣ ህዝብን ከህዝብ ጋር የሚያጋጭ እጅግ አደገኛና ዘረኛ ቅስቀሳ በመንዛት ላይ መሆናቸው ደጋግመን ገልጸናል ። ይህ ዘረኛ ቅስቀሳቸው ደግሞ የትግራይን ህዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር በማጋጨት ላይ ብቻ ያተኮረ አይደለም ። የትግራይ ህዝብንም ጭምር ውስጥ ውስጡን አውራጃን ከአውራጃ ፣ የድርጅት ኣባልን የድርጅት ኣባል ካልሆነው ጋር ፣ ተማሪን ከአስተማሪ ፤ ተማሪን ከተማሪ ወ.ዘ.ተ. በማጋጨት አንዱ በአንዱ ላይ ገብቶትም ይሁን ሳይገባው እንዲዘምት እየገፋፉትና እያሴሩበት ይገኛሉ ።

ይህ በትግራይ ህዝብ ማኸል የዘሩት አስቀያሚ የከፋፍለህ ግዛ መርዝ በማኸል አገርም በአዲስ መልክ ረቀቅ ባለ ዘዴ እያሰራጩት ነው ። ሰሞኑን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የታየው የተማሪዎች ንቅናቄ <u>የህዝብ ድምጽ ይከበር</u> የሚል ሰላማዊ ጥያቄ ሆኖ እያለ ፣ እነዚሁኑ የኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎችን በዘር እንዴት እንደከፋፈሉዋቸው ይኸው ከምን ጊዜም በላይ ቁልጭ ብሎ ወጥቷል ። ዛሬ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ ውስጥ ያሉት ተማሪዎች በአእምሮ ጎልምሰው በመውጣት ለአገራቸውና ህዝባቸው የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት ለመስጠት እንዲችሉ ሰልጥነው የሚወጡበት ሁኔታ በማመቻቸት ፋንታ ፤ አንዴ ስውር ሌላ ጊዜ ግልጽ የዘር ክፍፍል በማስተጋባት እያጣልዋቸው ይገኛሉ ። ከውጭ ሲታይ ተራ ገዢ ፓርትን የመደገፍና የመቃወም ጥያቄ

ሊመስል ይችላል ፤ ውስጡ ግን የረቂቀ የዘር መርዝ የታከለበት ከዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የማይጠበቅ አስቀያሚ መከፋፈል ነው ። በውነቱ ከሆነ ማንኛውም ዩንቨርሲቲ የደረሰ ተማሪ ይቅርና የ 1ኛ ደረጃ ተማሪም የለገሰ "መለስ" ዜናዊ ቡድን ከሃዲ፣ ሙሰኛ፣ ጸረ-ህዝብና ጸረ-ሃገር መሆኑ ይስተዋል ብሎ መገመት ኣይቻልም ። ግራም ነፈሰ ቀኝ ፣ የማፍያዎቹ የእነ ለገሰ ዓላማ ህዝብ የተፋውን ሥርዓታቸው ተማሪዎቹ ተባብረው ውድቀቱን እንዳያቀላጥፉት ለመቆጣጠር የቀመሩት የጮሌዎች ሴራ በመሆኑ ሁሉም እንዲነቃበትና ብሎም በአላፊው መንግስትና በነዋሪው ህዝብ መካከል ያለውን ሰፊ ልዩነት ጠንቅቆ በማጤን ለህዝባዊው ድል በጋራ መታገል ይኖርበታል ።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ባለፉት ሳምንታት የህዝብ ድምጽ ይከበር በማለት ተገቢ ዴሞክራሲያዊ ጥያቄ አንግበው የረሀብ አድማ መጀመራቸውና ከዚህ በተነሳም ለእስር ፤ ለድብደባና ለሞት መዳረጋቸው ዓለም አውቆታል ። ከዚህ በፊት ተማሪውን በጥይት ቀስፈው ለተወሰነ ጊዜ ጸጥ እንዳደረጉት ሁሉ ኣሁንም ያንኑ የለመደባቸው ኣረመኔያዊ ተግባር በመቀጠል ቤተ መንግስት ውስጥ መሽገው ለመሰንበት ያላቸውን ሕልም ማተግበር ይፈልጋሉ ። አፈናን ተሸክሞ የመኖር ዘመን እንዳበቃ የተገነዘቡት አይመስልም ፥ አሁንም የህዝብን ድምጽ ረግጦ መግዛት መግዛትን ቀጥለውበታል ፤ የአምባገነኖች የተለመደ ባሕርይ ይሉታል ይህ ነው ! በዚህ ላይ መብቴ ይከብር ብሎ በሰላም ጥያቄውን ያነሳው የአዲስ አበባ ከተማ ህዝብን ለማፈን ከዚህም ከዚያም የተሰባሰበ ልዩ ጦር በማሰማራት አዲስ አበባን አስከብበው ከሰነበቱ በህዋላ ፤ መጨረሻ ላይ የሰላማዊ ህዝብ ህይወት በጥይት እንዲቆላ አድርገዋል ። በየክፍለ ሃገሩም ተመሳሳይ ፋሽሽታዊ እርምጃ እየተወሰደ ይገኛል ። ይሁን እንጂ ህዝቡ ከንግዲህ ወዲያ በቃኝ ፣ መብቴን አላስነጥቅም ብሎ የአፈናው በረት ሰብሮ ወጥተዋል ። የነብር ጭራን አይዙ ፣ ከያዙም አይለቁ እያለ ነው ። ዴሞክራሲና አምባገነንነት ፤ መብትና አፈና ፤ ህዝብና ገዥዎቹ የለየለት ትንቅንቅ ተያይዘዋል ።
ሚና የሚለይበት ወቅት ላይ ደርሰናል ። ወደ ህዋላ መመለስ ፈጽሞ አይቻልም ።

እንግዲህ ይህ መግለጫ ለማውጣት ወዳነሳሳን ጉዳይ ስንመለስ ፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሰሞኑን የታሰሩ ወንድም/እህቶቻቸው ከእስር እንዲፈቱ ጥያቄ ከማቅረባቸውም በላይ በተለይ ለአቻዎቻቸው የትግራይ ተማሪዎች በዚህ ትግል ውስጥ በጎናቸው እንዲቆሙ የትግል ጥሪ ማስተላለፋቸውን አይተናል ። በመሠረቱ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች በአመለካከት እንጂ በዘር መለያየት ባልተገባቸው ነበር ። ዩኒቨርሲቲ የእውቀት መገበያ በመሆኑ ፤ በአመክንዮ የተደገፉ የተለያዩ አመለካከቶች መወያያ ፤ የአጠቃላዩን የአገራችን ችግር መነሻና መፍትሔ ላይ ያተኰሩ ጥልቅ ውይይቶች መናኸርያና የመፍትሔዎች ጠቋሚ ሓሳቦች ማፍለቅያ እንዲሆኑ ይጠበቃል ። ተከታታይ ሥርዓቶች የሥልጣን እድሜያቸውን ለማራዘም ሲሉ እየከፋፈሉን ቢቆዩም ሳይሳካላቸው ቀርቷል ። የዛሬዎቹም መከፋፈሉን በከፋ መልኩ እየተጠቀሙበት ቢገኙም ፤ ተማሪው የከፋፍለህ ግዛ ሴራቸው ላይ በሚገባ መንቃት ነበረበት እንላለን ። ከዚህ በፊት ከ300 በላይ የኦሮሞ ተማሪዎች ያለ ምንም ፍርድ ከአ.አ.ዩ ከነጭራሹ ሲባረሩ ተማሪው ተከፋፍሎ እንደነበረ ይታወሳል ። ችግሩ ይኸው ዛሬም ቀጥሏል ። በዚህም አያቆምም ፤ ነገ በተራው ሌላውን ያዳርሳል ። የዚህ ዓይነት ሴራ ጨርሶ ሊቆም የሚችለው ተማሪው በመብቱ ላይና ባገሩ ጉዳይ ላይ ሰፋ ያለ የጋራ ራእይ ኖሮት የሚደርሰውን ግፍ ተባብሮ ለመታገል ሲችል ብቻ ነው ። ከላይ እንደተጠቀሰው የአ.አ.ዩ ተማሪዎች ሃላፊነት የተሞላብት በጎ ሃገሪዊ ጥሪ አስተላልፏል ። በመሆኑም ተገቢ ኣወንታዊ ምላሽ ማግኘት ይገባዋል እንላለን ።

ተገቢና አዎንታዊ ምላሽ ማግኘት አለበት ስንል የትግራይ ተወላጅ ተማሪዎች ከራሳቹህ አልፎ በቤተሰብና ዘመድ አዝማዶቻቹህ ላይ ሊደርስ የሚችለውን የነለገሰና የነስብሓት ጭካኔ ምን ሊሆን እንደሚችል በመዘንጋት አይደለም ። ያላችሁበት ድርብ ውጥረትና ጭንቀት በሚገባ ይሰማናል ። ሰው መሆናቹህን እናውቃለን ። ይህንን የምንለው አንድ ቀን ከወገኖቻችን ጋር አብረን በመቆም ይህንን አስነዋሪ ኢ-ሰብአዊ ጭካኔ በመስዋእትነት

ማስወገድ ካልቻልን ፧ ምን ጊዜም መውጫ ሳይኖረን ለትውልዶች የሚተላለፍ ጥፋት እየተፈፀመ እንደሚቀጥል ስለምንረዳ ነው ። ከዚህ ለመውጣትና የራሳችንንና የወገናችንን መብት ለማስከበር እንድንችል በጋራ የመቆም ጥያቄ እጅግ አንገብጋቢ እየሆነ መምጣቱን መገንዘብ እንደሚያስፈልግም ልናሰምርበት እንገደዳለን ። ሌሎች ተማሪዎችም የትግራይ ተማሪዎች ያሉበት አጣቢቅኝን በመረዳት ጉዳዩን እጅግ በረቀቀ ዘዴ እንዲያስተናግዱት እያሳሰብን ፧ ነገር ግን ከየትም ወገን ይምጡ ከየት በተማሪ ስም ዩኒቨርሲቲው ውስጥ የተወሸቁትን ሰላዮችና ከፋፋዮችን ግን ያለ ምህረት እንዲያጋልጡ እንጠይቃለን ። ት.ዴ.ት የተማሪውን የራሱና የህዝብ መብት የመከበር ዴሞክራሲያዊ ጥያቄን ከልብ እንደሚደግፈውም ልናረጋግጥላቹህ እንወዳለን ።

በማያያዝም ተማሪው እንዲገነዘበውና እንዲገፋበትም የምናሳስበው ህዝባዊ የመብት ጥያቄ አለ ። ይኸውም የትግራይ ህዝብን የመምረጥ መብት የሚመለከት ነው ። ህወሓት/ኢህአዴግ ትግራይ ውስጥ ምርጫን መቶ በመቶ አሸነፍኩ እያለን ነው ። ይህ አባባል ምርጫ ትርጉሙን ቀየረ ወይ ? የሚል ጥያቄ ያስነሳል ። በበኩላችን ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን ያላሟላ ምርጫ ፍትሓዊ ሊሆን እንደማይችልና ኢህአዴግ ፍትሓዊ ምርጫ የማካሄድ ሥነ-ሓሳባዊ እምነት የሞራል ብቃትም ሆነ የሂልና ዝግጁነት ሊኖረው እንደማይችል ስንገልጸው የቆየን ሀቅ ነው ። ውጤቱንም አይተነዋል ። ያም ሆኖ ግን ትግራይ ውስጥ በሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች የታየ ዓይነት የይስሙላ ምርጫም ቢሆን አልተካሄደም ። ምርጫ ከተባለ ቢያንስ ከሁለት በላይ የሆኑ ተወዳዳሪ ወገኖች መኖር አለባቸው ። የተለያዩ ተወዳዳሪዎች ህዝብ ፊት ቀርበው ፕሮግራሞቻቸውን ለማስተዋወቅ መቻል አለባቸው ። የትግራይ ህዝብ ግን ይህ እድል ተነፍጎት እነ ለገሠ ዜናዊ ለብቻቸው ተወዳድረው በ100% አሸነፍን የሚሉበት መቀለጃ አድርገውታል ። በዚህም የትግራይ ህዝብና ሌላ ተወዳዳሪዎች የመምረጥና የመመረጥ መብታቸውን ተገፏል ። የትግራይ ህዝብ መብት መገፈፍ የመላው የኢትዮጵያ ህዝብ መብት እንደመገፈፍ የሚቆጠር መሆኑ ሊተኰርበት ይገባል ። ስለዚህም ተማሪው በቀጣይ ትግሉ ይህንን የመብት ጥያቄ አብሮ የሚያነሳው ታሪካዊ ግዴታው እንደሚሆን ለማሳሰብ እንወዳለን ። ባጭሩ በትግራይ ውስጥ ምርጫ ስላልተደረገ ፧ ምርጫ ይደረግ የሚል የህዝብን የመብት ጥያቄም እናስተጋባ ።

እዚህ ላይ ለዚህ የተማሪዎች ጥሪ መቅረብ ምክንያት የሆንው ምን/ማን ነው ? ተማሪውስ እስከዚህ ድረስና በዚህ መልክ ለምን ተከፋፈለ ? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመዳሰስ እንፈልጋለን ። ለኛ ሁለት ችግሮች ጎልተው ይታዩናል።

1ኛውና/ ዋነኛው፣ ከላይም እንደጠቀስነው የኢህኣዴግ ጠባብ ኣመራር ለራሱ ስልጣን ማቆናጠጫ ሲል የብሄረሰብ ፖለቲካ ፧ ጥላቻንና ቶክክርን ባነገበ መልኩ ህጋዊነት አልብሶ አንድነትን በሚሸረሽር አሰራር መጠቀሙ ነው ። በአገራችን ታሪክ ውስጥ ህዝብና ህዝብን በማጋጨት ስልጣን ላይ ለመቆየት ክፍፍልን በመብት ሽፋን ሕጋዊ አድርጎ የማዋቀር ስልትን የተጠቀመ አገዛዝ ስናይ የመጀመርያ ጊዜያችን ነው ። ከዚህ በፊት የነበሩ አገዛዞች የከፋፍለህ ግዛ ስልት ቢጠቀሙም ሕጋዊ ሽፋን ሰጥቶ በቅስቀሳ ጎልቶ እንዲታይ በማድረግ አልነበረም ። መጨረሻ ላይ የመንግሥቱ ኃይለማርያም አገዛዝ ህልውናውን ለማስጠበቅ ያቀረበው ከፋፋይ ጥሪም አልሰራለትም ፧ ዛሬም ይህ ሰንካላ የፖለቲካ ዘይቤ አይሰራም ። ለመላው ኢትዮጵያዊ ፧ ለትግራይ ህዝብም ሆነ ለተማሪውም ይጎዳዋል እንጂ ምንም አይጠቅመውም ። በርግጥ ጥቂት የኢህኣዴግ ካድሬዎች (የደርግ ካድሬ ሲያተራምስ እንደነበረው) ግብዝ ተልእኮ ይዘው እሳት ይጭራሉ ። እነዚህ በህዝቡ ስም እያላዘኑ ለስግብግብ ዓላማቸው የሚሽለኰለኩ የነለገሰ ጥቂት አሽከሮች ካብዛኛው ልበ-ንጹህ ተማሪ ለይቶ ማየት ያስፈልጋል ። እነዛ አሽከሮች ለእሳት መጫርያ የሚጠቀሙበት የጥላቻ ክብሪትን የሚያገኙት ከየት ነው ስንል ወደ ሁለተኛው በሽታ ይወስደናል።

2ኛው/ ልክ ከለገሰ ካድሬዎች ጋር የሚመሳሰሉ ጥቂቶች ፣ በህዝብና በዓፋኝ መንግስት መካከል ያለው ሰፊ ልዩነት ያልገባቸው ወይም እየገባቸ በስሜት የሚነዱ ፣ ከጭፍን የጥላቻ ፖለቲካ መውጣት ያስቸገራቸው የታሪክና የፖለቲካ መሃይማን የሚዘሩት ያልተገራ ስድብ አይሉት ዛቻ ሌላኛው ጠንቅ ነው ። የእነዚህ ዓይነቶቹ ተቆርቃሪ መሳይ ፧ የጥላቻ

ፊታውራሪዎች ሰዉን ወደ እነለገሰ ካምፕ እንዲጠጋ ምክንያት ከመሆን አልፈው የሚፈጥሩት ገንቢ ሥራ ወይም የሚሰነዝሩት ጠቃሚ ራእይ ባይኖራቸውም ፣ ከአቻዎቻቸው የለገሰ ካድሬዎች ጋር ጎን ለጎን እየተራመዱ በይዘቱ ተመሳሳይ የሆነ አፍራሽ መፈክር እያስተጋቡ ህዝቡን ለግጭት ይቀሰቅሳሉ ። ይህ አካሄድ ለኢትዮጵያ አይጠቅማትም ፤ ስለሆነም አምርረን እንዋጋዋለን ።

'ከሁለት ስሕተት በምንም ዓይነት መልክ አንድ እውነት አይወጣም' እንዲሉ በሁለቱም አቅጣጫ የተጠመደው አደገኛ ቅስቀስ ወደማንወጣው ቀውስ ሊከተን ስለሚችል የአደጋው አሳሳቢነት ከወዲሁ ተገንዝበን ፤ የለገሰ ዜናዊ አሽከሮችንና አስመሳዮቹን ነጥለን በማየት ፤ ህዝባዊና ዴሞክራስያዊ ዓላማችንን መሰረት አድርገን ለገንቢ ለውጥ በሕብረት እንቁም እንላልን ። ለዚህም የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ለጊዜው የፖለቲካ ልዩነቶቻቸውን በይደር በመያዝ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ ሁለቱን ከፋፋይ ኃይሎች በህብረት በመዋጋት አገራዊና ህዝባዊ ግዴታቸውን በብቃት እንዲወጡ ጥሪያችንን ዛሬም ደግመን እናስተጋባለን ። ከፋፋዮች ድል ሳይመቱ መቅደም የዴሞክራቶች ኃላፊነት ነው ።

በህዝቦች መካከል ጠብ የለም፤ ኣይኖርምም
በህብረታችን ኢትዮጵያ ታብባለች

ት.ዴ.ት 12 ሰኔ 1997

***ማስታወሻ፡

ወየነ ፡ ማለት አመጸ ፣ አበየ ብሎም አብዮት ሆኖ ወያኔ 1943 በትግራይ ለነበረው ህዝባዊ ንቅናቄ የተሰጠው ስም ነው። ስም ሳይቀር የሚሰርቁ፣ ሌቦቹ እነለገስን ወያኔ ብሎ መጥራት ማክበር ስለሚሆን ይቅርባቸው።

መለስ ፡ ያንድ ጀግና ደርግን አዲስ አበባ ሆኖ ሲፋለም የተሰዋ ኢትዮጵያዊ ስም ነው። ለገሰ ዜናዊ ተገባሩ የጀግና አይደለም፣ ዓላማውም ኢትዮጵያዊ ኣልሆነም። የጀግናው ስም ይቅርበት። አገር ይወቀው ፤ ለገሠ ይብቃው ።